

ክፍል 13

ክርስቲያን እንዲዋሽ ተፈቅዶለታል?

13-1

"ጎሽ አሳመነች ያንን ስልክ አንሽው። አሳበች ከሆነች የለችም አሁን ወጣ ብላለች በያት" አለች መሳይነሽ። አሳማኒች ስልኩን ብድግ አድርጋ "ሄሎ" ትላለች። እንደምነሽ አሳበች? መሳይነሽን ማነጋገር ትፈልጊያለሽ? ቆይ ጠበቂ፣ ላቅርብልሽ" ብላት ስልኩን ለመሳይነሽ ትሰጣታለች። መሳይነሽ አሳመነችን እየገላመጠች ስልኩን ተቀብላ ማነጋገር ጀመረች። ልክ ስልኩን እንደጨረሰች በቁጣ "አሳበች ከሆነች የለችም በይ አላልኩሽም ነበር?" አለቻት። አሳመነች ግን ረጋ ብላ "ክርስትያን ውሸት እንዲዋሽ ተፈቅዶለታል እንዴ እያለሽ የለሽም ብዬ መናገር ለህሊናዬ ይከብደኛልና ይቅርታ አድርጊልኝ፤ ከውሸት ጋር መተባበር አልችልም" ብላ መልስ ሰጠቻ። መሳይነሽም "እባክሽን ሕግ አታጥ ብቂ፤ የዳንነው በጸጋ ነው እንጂ "አድርግ" "አታደርግ" የሚለውን ትዕዛዝ በመጠበቅ አይደለም" ትላታለች። አሳመነችም "ስሚ ከሕግ ነጻ መሆን ማለት የመዋሸት ወይንም ኃጢአት የመሥራት ፈቃድ መቀበል ማለት አይደለም"። ሮሜ 6፣15 ላይ "እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስለአይደለን ኃጢአትን እንሥራን?" የሚለውን አላነበብሽም ትላታለች።

አሥረስ በአይሮፕላን ተሳፍሮ ናይሮቢ ይገባል። ናይሮቢ በገባ በ2ኛው ቀን ከስደተኞች ጽሕፈት ቤት ሄዶ በእግሩ ከኬንያ ጠረፍ እንደደረሰ ይገልጽና የስደተኛነት መታወቂያ ይቀበላል። አሥረስ ኬንያ በገባ በ6ኛው ወር ሁሉ ነገር ይሳካለትና ወደ አሜሪካ በስደተኛነት በቅርቡ ለመሄድ ይዘጋጃል። አሥረስን በቅርብ የሚያውቀው ክርስትያን ጓደኛውን ሊሰናበተው እቤቱ ይሄዳል። "አሥረስ ተሳክቶ ልህ አሜሪካ ለመሄድ መዘጋጀትህ ደስ ሲለኝ አንድ ነገር ቅር የሚለኝ አገር አለ። ይኸውም፣ አንተ ወደ አሜሪካ የምትሄደው ያልሆንከውን ሆኛለሁ ብለህ ዋሽተህ ነው፤ ለመሆኑ ክርስትያን እንዲዋሽ ተፈቅዶለታል እንዴ?" ብሎ ጠየቀው። አሥረስም ሲመልስ "እባክህን አትመጻደቅ እውነትን ይዜ ብቀመጥ ዘላለም ሳክ ነበር የምኖረው፤ አንተስ ይኸው ከመጣህ 4 ዓመት አልፎህ የለም? ምን አገኘህ? ተአምር ከሰማይ ይመጣል ብለህ ጠብቅ፤ ስለ ውሸቴ ጌታን ይቅርታ ጠይቄው ይቅርታ አድርጎልኛል" ይለዋል። "ስማ አስረስ አንተ የምታየው አሜሪካ መግባትህን ብቻ ነው። ሕይወት አሜሪካ መግባት ላይ ብቻ የተመሠረት አይደለም። ከገባህ በኋላ ምን እንደሚያጋጥምህ አታውቅም። ያ ሥፍራ ለአንተ በጎ ከሆነ ጌታ በምንም ዓይነት አይከለክልህም። ደግሞ "በኃጢአት ከሚገኝ ብልጽግና ይልቅ በጽድቅ የሚገኝ ድህነት ይበልጣል" የሚለውን ቃል አትርሳ" ሲል ይመልስለታል።

የብዙዎች ክርስትያኖችን ዕለታዊ ሕይወት ስነመለከት በእርግጥ ውሸት መዋሸት የተፈቀደ ይመስላል። ብዙዎች ዝሙት፣ በኃይል የሌላውን ሀብት መንጠቅ፣ መደባደብና መፈነካከት ኃጢአት ነው ብለው ስለሚያምኑ ራሳቸውን ከእነዚህ ኃጢአቶች ይጠብቃሉ። ውሸት ግን ትንሽ ኃጢአት ነው ብለው ስለሚገምቱ ለራሳቸው የመዋሸት ነጻነት ይሰጡታል።

ውሸትን የሚለማመዱ፣

1. ያልሆኑትን እንደሆኑ ይናገራሉ።

2. የራሳቸው ያልሆነውን በውሸት የራሳቸው እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ።
3. በሥራ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ባለመጠበቅ ጊዜ ይሰርቃሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ውሸት ምን ይላል?

1. "ሀሳትን የሚናገር አፍ ይዘጋል" (መዝ. 63፣11)።
2. "ሀሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም፤ በሀሰትም የሚናገር አያመልጥም" (ምሳሌ 19፣5)።
3. "ውሸተኛ ከንፈር ከእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወደዱ ናቸው" (ምሳሌ 12፣22)።
4. "በሀስተኛ ምላስ መዝገብ ማከማቸት የሚበን ጉም ነው" (ምሳሌ 21፣6)።
5. "እርስ በእርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፤ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፈችሁታልና" (ቆላ. 3፣9)።
6. "የሀሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው" (ራዕ. 21፣18)።

ውሸትን የተለማመዱ

1. አብርሃም

የእምነት አባቶች ተብለው ከሚጠሩት መካከል አብርሃም የመጀመሪያው ሰው ነው። አብርሃም ልጁን እስከ መሰዋት ድረስ ለእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅርና እምነት የነበረው ሰው ነበር። ይሁን እንጂ አብርሃም የራሱ የሆነ መንፈሳዊ ድካም ነበረበት። ይኸውም ውሸት ነበር። አንዴ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ በሕይወቱ ውስጥ የውሸት ፈተና ሲያጋጥመው እናያለን።

ሀ) "በምድርም ራብ ሆነ አብራምም በዚያ በእንግድነት ይቀመጥ ዘንድ ወደ ግብጽ ወረደ፤ ወደ ግብጽም ለመግባት በቀረበ ጊዜ ሚስቱን ሣራን እንዲህ አላት። አንቺ መልከ መልካም ሴት እንደ ሆንሽ እነሆ እኔ አውቃለሁ፤ የግብጽ ሰዎች ያዩሽ እንደሆነ ሚስቱ ናት ይላሉ፤ እኔንም ይገድሉኛል። አንቺንም በሕይወት ይተውሻል። እንግዲህ በአንቺ ምክንያት መልካም ይሆንልኝ ዘንድ ስለ አንቺም ነፍሴ ትድን ዘንድ እኅቴ ነኝ በይ" (ዘፍ. 12፣10-13)።

ለ) "አብርሃምም ከዚያ ተነሥቶ ወደ አዜብ ምድር ሄደ፤ በቃዴስና በሱር መካከልም ተቀመጠ፤ በጌራራም በእንግድነት ተቀመጠ። አብርሃምም ሚስቱን ሣራን እህቴ ናት አለ፤ የጌራራ ንጉሥ አቤሜላክ ላከና ሣራን ወሰዳት" (ዘፍ. 20፣1-2)።

2. ይስሃቅ

ውሸት መናገር እንደተላለፈ በሽታ ከአብርሃም ወደ ልጁ ወደ ይስሃቅ ተላለፈ። "ይስሃቅ በጌራራ ተቀመጠ። የእዚያም ስፍራ ሰዎች ስለ ሚስቱ ጠየቁት። እርሱም እኅቴ ናት አለ፤ የእዚያ ስፍራ ሰዎች ለርብቃ ሲሉ እንዳይገድሉኝ ብሎ ሚስቴ ናት ማለትን ፈርቷልና እርስዋ ውብ ነበረችና" (ዘፍ. 26፣6-7)።

3. ያዕቆብ

አብርሃም የጀመረው ኃጢአት በልጁ በይስሃቅ ላይ አላበቃም። አልፎ የልጅ ልጁ ከሆነው ከያዕቆብ ደረሰ። "ያዕቆብም አባቱን አለው፥ የበኩር ልጅህ እኔ ኤሳው ነኝ፤ እንደ አዘዝኸኝ አደረግሁ፤ ነፍስህ ትባርከኝ ዘንድ ቀና በልና ተቀመጥ፤ ካደንሁትም ብላ" (ዘፍ. 27፣19)። ያዕቆብ አባቱን እንደ ዋሸ ልጆቹ ደግሞ ዮሴፍን ለግብጽ ነጋዴዎች ከሸጡት በኋላ አውሬ በላው በማለት በፍየል ደም የዮሴፍን ቀሚስ በመቀባት ለአባታቸው ሰጡት። ውሸት ለሚናገረው ቀላል ኃጢአት ይምሰለው እንጂ ዋጋ ሳይከፍል አይቀርም።

.....